# ልማትን ከመቃወም ልክፍት ይጠብቀን!!

**ዳዊት ጋሞ - ከፓሪስ**

የታላቁ የኢትዮጲያ ህዳሴ ገድብ ግንባታ ይፋ ሆኖ ተግበራዊ እንቅስቀሳሴው ተጀምሯል። ህዝቡም ግድቡን ለማሰራት ተነሳሽነቱን ከዳር እስከ ዳር እያሳየ ይገኛል። ይህን ተከትሎ የተወሰኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በጉዳዩ ላይ መግለጫ አውጥተዋል።ከነነዚህም መካከል የተወሰኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስብስብ የሆነው መድረክ አንዱ ነው።

«መድረክ፣ መሠረታዊና የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ሁኔታ ያገናዘበ ልማትን መቼም አይቃወምም» በሚል ርዕስ ከሰሞኑ ያወጣው መግለጫ ግድቡን የመገንባት ተግባር የህዝቡን ኑሮ ለመለወጥ ቅድሚያ የሚሰጠው አይደለም፣ ለፕሮጀክቱ የሚወጣው ገንዘብ በሙሰኞች ስላለመበላቱ ጥርጣሬ አለኝ ይላል። ከዚህ ጋር አያይዞም የራሱን የፖለቲካ አጀንዳ ለግድቡ ግንባታ እንደቅድመ ሁኔታ አስቀምጧል። «ከግድቡ መገንባት አስቀድሞ ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር ኢህአዴግ ዝግጁ መሆን አለበት» በሚል።

የመድረኩ ፕሬዚዳንት አቶ ገብሩ አስራት በግድቡ ላይ ያላቸውን ቅሬታ ገልፀዋል። «ኤሌክትሪክ ማመንጨትን ብቻ ማዕከል ያደረገው የአባይ ግድብ ፕሮጀክት ግልፅ አይደለም፣ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው የመስኖ ስራዎችን ያካተተ ፕሮጀክት መሆን ነበረበት ብለዋል።

መድረክ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ላይ ያቀረበው መቃወሚያ ሁለት ዓይነት ገፅታ አለው። የመጀመሪያው፣ የግድቡን ፕሮጀክት አላማና የግንባታውን አፈፃፀም ይመለከታል። ሌላኛው፣ ከፓርቲው የፖለቲካ አቋም ጋር ይያያዛል። የመጀመሪያውን የተቃውሞ ነጥቦች ለግዜው ገታ አድርገን በቅድሚያ «ኢህአዴግ

ግድቡን ከመስራቱ በፊት ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር ዝግጁ መሆን አለበት …» በሚል እንደ ቅድመ ሁኔታ የቀረበውን ጥያቄ እንመልከት።

መድረክ ለግድቡ ግንባታ መሟላት አለበት በሚል እንደ ቅድመ ሁኔታ ያስቀመጠው ይህ « ብሔራዊ መግባባት» የሚለው ጉዳይ ከሽግግር መንግስት ወቅት አንስቶ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲያቀርቡት የኖረ ፕያቄ ነው። ጥያቄው በተደጋጋሚ ይቅረብ እንጂ፣ አሁንም ድረስ የጉዳዩ ምንነት በግልፅ መረዳት አይቻልም።

ጥያቄው አገር ውስጥ ሕጋዊ ሆነው ከሚንቀሳቀሱት ይልቅ፣ በአብዛኛው በውጭ አገራት «ተቃዋሚ ነን» ብለው ራሳቸውን በፈረጁ ቡድኖች የሚቀርብ መሆኑ፣ የጥያቄውን ምንነት በግልፅ መረዳት እንዳይቻል ያደረገ አንዱ ምክንያት ነው።

እርግጥ በውጭ ከሚንቀሳቀሱት ተቃዋሚ ነን ባይ ቡድኖች የሎጂስቲክስና የፋይናንስ ድጋፍ እየተደረገላቸው በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የተወሰኑ ፓርቲዎች አልፎ አልፎ ይህንኑ ጥያቄ ሲያስተጋቡ ተደምጠዋል።

ሌላው የጥያቄውን ምንነት በግልፅ ማወቅ እንዳይቻል ያደረገው ምክንያት፣ አገሪቱ የምትመራበት ሕገመንግስት እና ይህንኑ፣ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ሌሎች ሕጎች እያሉ የአገርን ጉዳይ እንደተወሰኑ ቡድኖች ጉዳይ በስምምነት እንዲወሰን የሚቀርብ ጥያቄ መሆኑ ነው።

ያም ሆነ ይህ፣ «ብሔራዊ መግባባት» አንዳንዴም «ብሔራዊ ዕርቅ » የሚባለውን የተቃዋሚዎች ጥያቄ ምንነትና አላማ ብዙ ጥናትና ምርምር ሳያስፈልገው መነሻና ግቡን በቀላሉ መገመት ይቻላል። የመጀመሪያው ግምት፣ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ቡድኖች አንድ አይነት አቋም ለመያዝ ይስማሙ፣ በዚህ ስምምነት መሰረት መታረቅ ይገባቸዋል የሚል ነው።

እርግጥ መስማማት፣ አንድ አይነት አመለካከት መያዝ በራሱ ችግር አይደለም። የዚያኑ ያህል የተለያዩ ወገኖች «ትክክል ነው» ብለው እንዳመኑበት የተለያየ

አቋምና አመለካከት መያዛቸውም እንደዚያው። ልዩነታቸውን አቻችለው አመለካከታቸውን በሰላማዊ መንገድ የማራመድ መብት አላቸው። የኢ.ፌዴሪ ህገ መንግስት፣ በዴሞክራሲያዊ መብት ደንጋጌው ይህንኑ በግልፅ አስፍሯል።

የኢትዮጵያ ህገመንግስት ማንኛውም ዜጋ ያመነበትን አመለካከት የመያዝ፣ አመለካከቱን በግልና ከሌሎች ጋር በቡድን ተደራጅቶ በሰላማዊ መንገድ የማራመድ ፣ በአመለካከትና በአቋሙ ለፖለቲካ ሥልጣን የመፎካከር መብትን በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጧልና።

በአገር ውስጥ በተለያየ አመለካከት የተደራጁ ፓርቲዎች ህጋዊ እውቅና ተሰጥቷቸው አቋማቸውን በሰላማዊ መንገድ ማራመድ ያስቻላቸው ይህ በዴሞክራሲያዊ መርህ ላይ የተመሰረተው ህገ መንግስታዊ መብት መሆኑ እውነታ ነው።

በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአመለካከት ተደራጅቶ አመለካከትን በሰላማዊ መንገድ በይፋ የማራመድ መብት ያረጋገጠ ሕገ መንግስት ቢኖርም፣ ይህን መብት ከመጠቀም ይልቅ «የእኔ አመለካከት የበላይ ነው፣ በሐይል መፈፀም አለበት…» የሚል ፅንፈኛ አቋም ይዘው በውጭ አገር የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችና ቡድኖች መኖራቸውን ልብበሉ።

የፖለቲካ አመለካከትና አቋማቸውን በኃይል ለማስፈፀም ጦርነት ያወጁ፣ በሽብር ጥቃት መንግስትና ህዝብን አንበርክከው ስልጣን ለመያዝ፣ አስተሳሰባቸው ህዝብ ላይ ለመጫን ወስነው የሚንቀሳቀሱ መኖራቸውንም እንዲሁ አንዘንጋ ። የለየላቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ላይ ተለጥፈው የሽብር ጥቃቶችን ሲፈፅሙ የቆዩ መኖራቸውንም አንዘንጋ።

እንግዲህ፣ የኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግስት ከ1983 ዓ.ም በፊት የነበረውን አመለካከትንና አቋምን በይፋ የማራመድ መብትና ነፃነት በአዋጅ የተጣሰበትን የፖለቲካ ስርዓት ሽሯል። ማንም ግለሰብ የፈቀደውን የፖለቲካ አመለካከት የመቀበል፣ የማራመድ፣ ከመሰሎቹ ጋር የመደራጀት መብት አለው።

ማንኛውም ግለሰብ ወይም ቡድን በተቀበለውና በሚያራምደው የፖለቲካ ምክንያት አይታሰረም፣ አይገረፍም፣ አይገደልም። ይህ ቅድመ 1983 ዓ.ም አመለካከትን ለማራመድ ብቸኛው አማራጭ የነበረውን የኃይል ትግል፣ የፈጠረውን ጦርነትና የህዝብ ዕልቂት አስቀርቶ፣ ለየትኛውም አመለካከት አራማጅ በነፃነት ሃሳቡን የማራመድ መብት ሰጥቶ ሰላም እንዲሰፍን አድርጓል።

በዚህም ምክንያት የተለያየ ማንነት ያላቸው የኢትዮጵያ ብሔሮችና ብሔረሰቦች፣ እንዲሁም የተለያየ አመለካከት አራማጅ ግለሰቦችና ቡድኖች ተከባብረውና ተቻችለው በሰላም መኖር ችለዋል። ከዚህ የተለየና የተሻለ አገራዊ መግባባት፣ ከዚህ በላይ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ምህዳር የለም።

በአንድ የጋራ አገር ላይ መግባባት ሰፍኖ ህዝቡ የፈቀደውን አመለካከት ተቀብሎ ለተመቸው በውክልና የመንግስት ስልጣን እየሰጠ በሰላም እንዲኖር፣ ከርሞ የተሻለ ህይወትን ተስፋ እንዲያደርግ የሚያስችል ፖለቲካዊ ሁኔታን ያረጋገጠው አሁን የምንኖርበት ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ነው።

«በዚህ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት መኖር አይመቸንም» ብለው አገር ጥለው ኮብልለው በፈረንጅ አገር በሞቀ ኑሮ ውስጥ የሸፈቱ አሉ። እነዚህ እንግዲህ፣ ሕገ መንግስቱ የፈጠረውን ዕርቅና መግባባት ያልተቀበሉ ናቸው። ማንም ህገ መንግስቱን ተቀበል ተብሎ ሊገደድ ስለማይችል ያለመቀበል መብት አለው። ህገ መንግስቱን አለመቀበል ግን፣ ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የመጋፋት መብት አያስገኝም፤ድርጊቱም በወንጀለኝነት ያስጠይቃል።

እናም ከዕርቁ ውጭ የሆኑት፣ ሕገ መንግስቱን ያልተቀበሉና፣ የራሳቸውን አቋም ከሌሎች ሁሉ አስበልጠው የበላይ መሆን አለበት - በኃይልም-ቢሆን የሚሉ ዕርቅ አሻፈረኝ ባይ ፅንፈኞች ብቻ ናቸው።

ሌላው ከዚሁ «ብሔራዊ መግባባት» አንዳንዴም «ብሔራዊ ዕርቅ» ከሚለው ጋር የሚነሳው ጥያቄ ዋና ባለጉዳይ፣ ኢ.ህአዴግ መሆኑ ነው። ኢ.ህአዴግ እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ከሕገ መንግስቱ ውጭ ከማንም ወገን ጋር በመግባባት አገራዊ ጉዳይ ላይ

ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው አካል አይደለም። አገራዊ መግባባትን የሚመለከት ጥያቄ መነሳት ቢኖርበትም እንኳን፣ መጠየቅ ያለበት በህገ መንግስቱ መሰረት በህዝብ ውክልና ስልጣን የተረከበው መንግስት ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን የአገሪቱን አንድነት ማስጠበቅ ያስቻለ፣ በእኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሰረተ ብሔራዊ እርቅ ሰፍኗል። ይህ ብሔራዊ እርቅ አገራዊ አንድነትና ሰላም ፈጥሮ፣ የመንግሥትና የህዝብ ትኩረት ህዝቡን ከድህነት አላቆ ወደተሻለ ህይወት የሚያሸጋግር የልማት አጀንዳ እንዲሆን አስችሏል።

እርቅ እምቢ ያሉት ደግሞ፣ «እወጋችኋለሁ፣ በሽብር ጥቃት እጃችሁን ጠምዝዤ አመለካከቴን እንዳትቀበሉ አደርጋለሁ፣ የግል ጥቅሜን በበላይነት አስጠብቃለሁ…» እያሉ ከፈረንጅ አገር እያቅራሩብን ነው።

አገር ውስጥ ህገ መንግስታዊው መብት ባስገኘው ዕድል እየተንቀሳቀሱ የፈረንጅ አገሮቹን ሽፍቶች ቀረርቶ መሀከላችን ሆነው የሚያስተጋቡም አሉ። አገራዊ እርቅ በፈጠረው የፖለቲካ ሜዳ ላይ ቆመው፣ «የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከመገንባቱ በፊት እንታረቅ» በሚል በመድረክ የቀረበው ጥያቄ የዚህ ማሳያ ነው። መድረክ «ስለየትኛው ፀባችን ነው የምንታረቀው?» ተብሎ ቢጠየቅ ምን ምላሽ ይሰጥ ይሆን?

የአባይን ግድብ ከመሥራታችሁ በፊት ብሔራዊ መግባባት /ዕርቅ ያስፈልገናል በሚል እንደ ቅድመ ሁኔታ የቀረበው ጥያቄ፣ ቀድሞውንም እርቅ እምቢ ብሎ የፈረጠጠ እንጂ ባለመግባባት የተጣላ ስለሌለ ጥያቄው መነሳት የሌለበት መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ሊያስተውለው ይገባል። የኢትዮጵያ ህዝብ የዘላለም ምኞት ሆኖ የኖረውን የአባይን ግድብ ለመሥራት የቀረበ ዕቅድን ለመተግበር እንደ ቅድመ ሁኔታ የቀረበው ይህ ጥያቄ አሳዛኝም አሳፋሪም ነው።

መድረክ ግድቡን በሚመለከት በመግለጫው ላይ ባቀረባቸው ዕቅድና አፈፃፀም ላይ ያነሳቸው ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ ማደናገሪያዎች ናቸው፡፡

ዋነኛው ጥያቄ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት አቋማቸውን በኃይል እንዲቀበል የሚፈልጉ ኢ-ዴሞክራሲያዊ አመለካከት ያላቸው ያረጀና በመሞት ላይ ያለ አመለካከት አራማጅ ስደተኛ ታጋዮች የፖለቲካ ዓላማን ለማሳካት የቀረበው የብሔራዊ መግባባት የተሰኘ ትርጉም አልባ ባዶ ጥያቄ ነው፡፡ ‹‹

መድረክ መሠረታዊና የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ሁኔታ ያገናዘበ ልማትን መቼም አይቃወምም›› በሚል በአባይ ግድብ ግንባታ ላይ ያቀረበው ቅድመ ሁኔታ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ልማትን ከማሰናከል መቼም ወደ ኋላ እንደማይል ከማመላከት ያለፈ ውጤት አያስገኝለትም። መግለጫው ከወጣ በኋላም ቢሆን ህዝቡ ለግድቡ ግንባታ እየሰጠ ያለው ምላሽ ለዚህ በቂ አስረጂ ነው።

የአገሪቱ ባለቤት፣ የመንግሥት ሥልጣን ብቸኛ ምንጭና ባለቤት የሆነው ህዝብ አሁንም ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የድጋፍ ስሜቱን እየገለፀ ነው። የገንዘብ ድጋፍና ልገሳም እያደረገ ነው።

መድረክ ከዚህ ቀደም መንግሥትና ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ በአባይ ጉዳይ ላይ ቁርጠኛ አቋም የላቸውም እያለ ሲቃወም እንደነበር የኢትዮጵያ ህዝብ ያስታውሳል። መንግስት በጉዳዩ ላይ ቁርጠኛ አቋም እንዳለው ብቻ ሳይሆን፣ በተግባርም ሲያሳይ ደግሞ ተግባራዊ እርምጃው አስጠላው፣ እናም ተቃወመው።

መድረክና በሥሩ ያሉት ፓርቲዎች ለአገሪቱ የሚያዋጣው ኢንዱስትሪ መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው ሲሉ እንደነበርም ይታወቃል። መንግሥት የአምስት ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አውጥቶ፣ እንቅስቃሴ ጀምሯል። ከአምስት ዓመት በኋላም ኢኮኖሚውን ኢንደስትሪው እንዲመራ ለማስቻል፣ ለኢንደስትሪ መኖርና ማደግ ወሳኝ የሆነውን የኤሌክትሪክ ኃይል በከፍተኛ መጠን የሚያመነጭ ግድብ ለመገንባት ተነሳሰቷል።

መድረክ በፊናው «የኤሌክትሪክ ኃይል ቅድሚያ የሚሰጠው አይደለም» ሲል የግድቡን ግንባታ ተቃወመ ኃይል- ኢንዱስትሪ ያለኤሌክትሪክ ኃይል ይንቀሳቀስ ይመስል፡፡ መድረክ ስልጣን ላይ ወጥቶ ቢሆን «አሁኑኑ ኢኮኖሚውን ካልመራ» ያለውን ኢንዱስትሪ በምን የኤሌክትሪክ ኃይል ሊያንቀሳቅሰው ነበር?

«ለግድቡ ግንባታ የሚውለው ገንዘብ በሙሰኞች ሊመዘበር ይችላል» የሚል ስጋት እንዳለውም መድረክ ገልጿል፡፡ ለግድቡ ግንባታ የሚያስፈልገው ወጪ በመንግሥት የካፒታል በጀት ሥር ስለሚያዝ፣ እንደማንኛውም የመንግሥት በጀት በጥብቅ የቁጥጥር ሥርዓት ስር የሚያልፍ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ግድቡን ለማስገንባት ከተለያየ የህብረተሰብ ክፍል - ከሃየማኖት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች… የተውጣጡ አባላትን ያካተተ ምክር ቤት እስከ ወረዳ ድረስ እየተደራጀ ነው። ህዝቡ የሚያስገነባውን ግድብ የስራ ሂደት በበላይነት የሚከታተለውና የሚቆጣጠረው ይህ አካል ነው። በመሆኑም ለምዝበራ ይጋለጣል ወይም የተጋለጠ ነው የሚያስብል አንዳች የተለየ ነገር የለም፡፡

መድረክ ይህን ያስባለው፣ መንግስት ለግድቡ ግንባታ የሚያስፈልገው ገንዘብ ከውጪ ምንጭ ማግኘት ባለመቻሉ ህዝቡ ያለውን ጥሪት ሀብቱን ምንም ሳይሳሳ ለግድቡ ግንባታ መለገስ ስለጀመረ ይህን ለማደናቀፍ በማሰብ ይመስላል። ህዝቡ በዚህ ወሬ ውዥንብር ውስጥ ገብቶ የልገሳ እጁን እንደማይሰበስብ ቢረዱ እንዴት መልካም በሆነ ነበር።

እናም «መድረክ የኢትዮጵያን ልማት መቼም አይቃወምም ወይንስ መቼም ቢሆን ከመቃወም ታቅቦ አያውቅም እንበል? ልማትን ከመቃወም ልክፍት ይጠብቀን!!